# ሰነፍ ቢመክሩት ውሀ ቢወቅጡት ከመባል ያድነን

ሀማ ቱማ

የሀገርና የወገንን ዋና ዋና ጥቅሞች ለማስከበር ህይወታቸውን የሰጡ ጀግና ሰማዕት አርአያነት ተረስቶ ዛሬ ፖለቲካው ለራሱ አያውቅ ጠንቋይ ሊባሉ በሚገባቸው ተጨናንቆ የሀገርና የሕዝብ መከራና ሰቆቃ ተባብሶ ይገኛል። የሀገራችንን የወደፊት ዕጣ ለባዕድ መስጠቱ ጅልነት ነው በሚልና የአሜሪካው አዲስ ፕሬዚዳንት ለሀገሩ ጥቅም የቆመ እንጂ የኢትዮጵያ ቤዛ አይደለም ብዬ ትችት በማቅረቤ ማንታቸው ግልፅ ያልሆነ ኢትዮጵያውያን ውጉዝ ከመ አርዮስ ሁን፣ እንጦርጦስ ያውርድህ፣ ኦባማዬን ለቀቅ እያሉ የዘመኑን ኢ ሜይል መልዕክት አዥጉድጉደውብኛል። ሞኝ መካሪውን ባለጌ አክባሪውን አይወድም የተባለውን ያስታውሰኛል።

ሕዝብ የራሱን ሀገር መጠበቅ አለበት ተብሏል። ማንም ሀገር ለሌላው ጥቅም ሲል መስዋዕትነትን አይከፍልም። ጣልቃ ከገባም ለራሱ ብሔራዊ ጥቅም ብቻ ነው። በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ጊዜ የእንግሊዝ ወታደሮች አዬውን ይዘው ኢትዮጵያ የገቡት ኢትዮጵያን ለመጥቀም እንደልነበር ሳይውል ሳያድር ሀገራችንን ሊቆጣጠሩ ሲጥሩ የታየ ጉዳይ ነው። የታንዛኒያ ወታደሮች ዩጋንዳን ወረው ጨቋኙን ኢዲ አሚን ሲያባርሩ የራሳቸውን ጥቅም አስጠባቂ ኦቦቴን መልሰው ከስልጣን ማስቀመጣቸውና ዩጋንዳንም መበዝበዛቸው ይታወቃል--ኦቦቴ ከአሚን ባልተናነሰ የዩጋንዳን ሕዝብ ፈጅቷል። አሜሪካኖች በቪየትናም ትላንትና፣ በኢራቅና አፍጋኒስታን ዛሬ ለሀገሬው አስበው እየሞቱለት ነው የሚሉ ካሉ መቸም ሳይጨፈኑ ሊሞኙ የቆረጡ ብቻ ናቸው። ወያኔም ሶማሌን የወረረው ለሶማሊያ ሕዝብ ጥቅም ቀርቶ ለኢትዮጵያም ሕዝብ ጥቅም አልነበረም--ያደረሰውን ጥፋትም ዓለም ታዝቧል። በአጭሩ ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ እንዲሉ ሕዝብ ለገዛ ሀገሩ ሊሰዋ ካልተነሳ ማንም ሀገሩን ነፃ አያወጣለትም፡3 ይህን መሰረታዊ ሀቅ መረዳት ያቃታቸው ዜጎች ግን ነጋ ጠባ ባዕዳን--እንዲያውም አንዳንዶቹ የኢትዮጵያ ጠላቶች የሆኑትን-- ሲማጠኑና እርዱን ብለው ሲወተውቱ ይደመጣሉ። በአሜሪካ ጥቁር ሰው ፕሬዚዳንት ብሎ መመረጡ ታሪካው መሆኑ እንዳለ ሆኖ ግለሰቡ አሜሪካዊ እንጂ ሌላ ባለመሆኑ የተመረጠው የአሜሪካንን ጥቅም በቅድሚያ ለማስጠበቅ ነው። በምርጫ ወቅት ተወዳዳሪዎች ከሰማይ ዳቦ እናወርዳለን ማለታቸው የሚጠበቅ ቢሆንም አዲስ የፖለቲካ መስመር እንቀይሳለን የሚለው አፍሪካን በተመለከተ አሮጌውን ፖለቲካ አዲስ ብሎ ሰይሞ መቀጠል መሆኑን በቢል ክሊንተንም ጊዜ ያየነው ነው። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሂላሪ ክሊንተን በአሁኑ ጊዜ በአፍሪካ የምታደርግወም ጉብኝት ይህንኑ ያሳያል። በሙስና የተጨማለቁትን የኮንጎውን ካቢላ፣ የአንጎላውን ዶስ ሳንቶስ፣ የኬንያውን ኪባኪና ናይጄሪያን የምትጎበኘው መስመር ለውጡ፣ የሕዝብን መብት አክብሩ ብሎ ለመከራከር ሳይሆን በተለይ ሀብታም ከሆኑት ሀገሮች (ኮንጎ፣ናይጄሪያ፣አንጎላ) ጋር የንግድ ግንኙትን ለማጠናከር ነው። አሜሪካ 26 በመቶ የዘይት ፍጆታዋን የምታመጣው ከአፍሪካ ነው። ወርቅ፣

አልማዝ፤ ዩራኒየም፤ኮልታን፤ቡና ፤ካካዎ ወዘተ የሚጫነው ከአፍሪካ ነው:: በመሆኑም ከኢክዋቶሪ ያል ጊኒ እስከ አንጎላና ኮንጎ ያሉትን አምባገነኖች እሹሩሩ ማለቷ ቀጣይ ነው:: አሜሪካ ራሷ የኮንጎን ማዕድን ውጤት በመፈለጓ ነው የምስራቅ ኮንጎ ሕዝብ መከራ ተባብሶ፤ ከመቶ ሺ ያላነሱ ሴቶች የተደፈሩትና ከ 5 ሚሊዮን ያላነሱ የኮንጎ ተወላጆች ያለቁት::ክሊንተን የተቃቀፈችው መሪ ካቢላ ወታደሮች የዚህ ግፍ ዋነኛ ተጠያቂ መሆናቸው ለማንም ስውር አይደለም::መለስም አሜሪካ ባዘዘው ይጣዳልና ከፍርፋሪው ድጋፍ ይቋደሳል፤የኦባማው ባልስልጣን ጆኒ ካርሰን ይህን ግብዝ አረመኔ ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲን ያመጣ ብሎ ማወደሱ በባዶ አይደለም::

የአንድ ሀገር ሕዝብ ጎንበስ አንገት ደፋን ትቶ፤እምቢኝና አመፅን አስቀድሞ መገኘት ግዴታው ነው:: አምላክ ይጠብቃቸው ብሎ በጎችን ደጅ አያሳድሩም-- ከተበሉ ጥፋቱ የባለቤቱ ነው:: ሀገርም በወረበላዎችና ገንጣዮች ስትቦጫጨቅ ከንፈርን እየመጠጡ ወይም የባዕድ ነፃ አውጪ እየጠበቁ መቀመጥ ደግሞ ከስህተተም በላይ ኃጢያት ቢባል ማጋነን አይሆንም:: የሕዝብን መብት እናስከብራለን፤ ሀገሪቷንም እንጠብቃለን ብለው የተነሱ የፖለቲካ ድርጅቶችም የሀገራቸ ው፤የአካባቢውና የዓለም አቀፉ ሁኔታ ባዳ ሆኖባቸው፤ከምስጢረ ሥላሴ በባሰ ረቀባቸው፤ ወዳጅና ጠላትን መለየት ተስኗቸው ነጋ ጠባ ድርሳነ ኦባማን ቢያነበንቡ ብሩህ ቀን መቸም የሚመጣ አይሆንም:: ተጨባጩን ሁኔታ በሚገባ ሊረዱ ከቻሉም ከሚከተሉት የትግል ግብ አንፃር ምን መደረግ አለበት፤ ከማን ጋር ማበር መተባበር ግድ ይሆናል ለሚሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስን መስጠት ይችላሉ:: ስለዚህም ከባዕዳን በፖለቲካው መስክ ድጋፍ ለማግኘት መጣርና ሁሉንም ግዳጅና ስራ ለነሱ አሳልፎ ሰጥቶ ነፃነትን ከአሜሪካና ሌላ ቦታ መጠበቅ የተለያየ ጉዳይ መሆኑን ሊገነዘቡ ይችላሉ ማለት ነው:: ሞኝ አሞራ የአባቱ ዋሻ ይጠፋዋል እንደተባለው የሀገር ጠላት ተረስቶ ወዳጅ የሚባልበት ሁኔታም ያከትማል ማለት ነው:: ለዚህም ነው ኦባማዬ ኦባማዬ በልኩና በቦታው (በዚያው ሰውዬው ባለበት ) ሆኖ የኢትዮጵያን ህልውናና ጥቅም በተመለከተ ግን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ሌላ ለሀገሩ የሚቆረቆር አለመኖሩን በጊዜ መረዳት የሚያስፈልገው:: ለኢትዮጵያ መሰዋት ያለባቸው ኢትዮጵያውያን ናቸው እንጂ አሜሪካ ዕድሜ ለኦባማ መጥቶ ይሞትልናል ብሎ መጠበቁ ኢትዮጵያዊ ጠባይምታሪክም አይደለም:: የሙሶሊኒ ፋሺስት ጦር ሀገራችንን ሲወር አርበኞች ጦር ጋሻ፤ አልቤን መውዜር፤ ሀገር ፍቅራቸውን ይዘው ተነሱ እንጂ ያውም በጊዜ ያልመጣን የባዕድ እርዳታ አልጠበቁም:: ጣሊያን ኢትዮጵያን ሲወር ምዕራብ ሀገሮ ች ደግፈውታል:: ሕዝብ በትግሉ ሀገሩን ሊያስከብር ከተነሳና በመስዋዕትነቱ መቁረጡን ካስተጋ ባ አዳማጭና ረዳም ሊያገኝ ይችላል:: ካንጀት ካለቀሱ እምባ አይገድም፤ደፋርና ጢስ መውጫ አያጣም ሲባል እንደነበረው ሁሉ ሕዝብ ቆርጦ ከተነሳ ለሀገሩ ስርየት መፍትሔን ያገኛል::

ይህ እውን ይሆን ዘንድ መስዋዕትነትን መድፈርና መክፈል የግድ ነው:: ዛሬ ታሪክን እንደ ሰካራ ም መኪና ነጂ የሚገጩና የሚጨፈልቁ በዝተዋል:: የሀገራቸውን ታሪክ ማወቅ ሲገባቸው አሉባ ልታና ክለሳን የሚያቅፉና የሚነዙ ጥቂቶች አይደሉም:: የታሪክ መምህር ነን ባዮችም ከዚሁ

ጥፋት ነፃ ሆነው መገኘት አልተቻላቸውም:: ለምሳሌ በቅርቡ አንድ አወቅኩ ባይ ሲፅፍ የሕዝብ የየካቲት አብዮት መንግስቱን ለስልጣን አበቃው ብሎ የሌባውን ወንጀል በሕዝብና በአብዮቱ ላይ ይጭናል:: ያ አረመኔ ስርዓት በሕዝብ ላይ ያወረደውን ሽብርና ፍጅትም ሽፋፍነው ትዝታቸ ውን ዛሬም ወንጀላቸውን በመከላከል ሞልተው በመፅሀፍ መልክ የሚያቀርቡ ብቅ ብቅ ብለዋል:: በዛሬው ዋና ጠላት ላይ ትኩረት ይደረግ መባሉን በሞኝነት የወሰዱ እነዚህ በሀገር ውስጥና ባዕድ ሀገርም ያሉ በደም የታጠቡ ሽብርተኞችና ወንጀለኞችን ትኩረት ሰጥቶ መታገልና ማጋለጥ አስፈላጊ እየሆነም መጥቷል:: ይህ ታሪክን የመበረዙ ጥቃት ለሀገርና ለወገን የተሰዉትን በማክቸ ልቸል ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የትግልም ሆነ የፖለቲካ ይዘቱ ጨቅይቶ ሀቀኛ ገፅታው የሚታይ አልሆነም:: ሀገር ማዳኑ ተጋድሎ መስዋዕትነትን ይጠይቃል:: አባ ገብረ መድህንን ሳይሆን አቡነ ጴጥሮስን፤ ክህደቱን ሳይሆን እነ ወብሸት ረታን፤ ምህረት ጠያቂውን ሳይሆን እነ ተስፋዬ ደበሳይ ን፤ ተካልኝና ሙሉጌታ ዜናን፤ ዳሮና ፅጌን ይፈልጋል:: ለሀገር መሞት ህይወት ዳግም ትንሳዔ ልደት የሚሉትን ይሻል:: ኦባማ አድነን ባዮችን ሳይሆን ፋኖ ተሰማራ በዱር በገደሉ ትግሉ እንዲ ጎመራ የሚሉ ጀግኖችን የት አሉ ይላል::

የፖለቲካና የተቃውሞ ይዘቱ ጎርንቶ ተገኝቷልና ዛሬ ካለው ስርዓት ዋነኛ ተጠቃሚዎች የስርዓቱ ን ውድቀት ፈላጊዎች መስለው መገኘታቸው እየታየ ነው:: ከንቱ!! በተለጣፊና በተቃዋሚ ድርጅት መሀል ያለው መሰረታዊ ልዩነት ከተድበሰበስ መጨረሻው ከቶም አያምርም:: ሕዝብም በተለይም ከተሜው፤ ንዐስ ከበርቴውና በየባዕድ ሀገሩ ያለው ይህን ልዩነት መረዳት አቅቶት ለፎከረ ሁሉ ካጨበጨበ ፤ ገንዘቡን ከለገሰ ፤የትላንት ፀረ ሕዝቦች ዛሬ ታጋይ ተቃዋሚ ነን ሲሉት ንስሐ ይቅደም ካላለ ፤ ከመ ቅፅበት የትናንት ወያኔን የዛሬ አርበኛ ማለትን ካልተው፤ በራሱ ላይ መከራን በማምጣት ቢከሰስ ቢወቀስ ሊቀበል ይገባዋል:: ሕዝብ እንደ ወያኔ ባለሁለት ጉድጓድ ዓይጥ አይደለምና ላለችው አንዲት ሀገር ህይወቱን ሊለግስ ሲነሳ በደንባራ በቅሎዎች ሊመራ አይገባውም:: ፀሐዩ ንጉሥ፤ ጌቶች፤ ልዑል ፤ ራስ፤ ደጃዝማች ብሎ ከመሬት መደፋቱ ዛሬ ዶክተር፤ ፕሮፌሰር ኢንጂኔር ዳኛ-ጠበቃ በሚል ተተክቶ ራሱን በጭፍን ለግለሰቦችና በትግል ተፈትነው ወኔያቸውንና ቁርጠኝነታቸውን ላላስመሰከሩ የመገዛት ባህል መወገድ አለበት:: የዴሞክራሲ ትግል አፋዊ ዘመቻ ሳይሆን በትግሉም በራሱ ይዘትና አካሄድ ለውጥን ያዘለ መሆን አለበት:: ለለውጥ ቆመናል እያሉ ስገዱልኝ ማለት፤ ትምክህት ጥበት ማንፀባረቅ፤ ለፍቶ አደሩን ህዝብና ሴቶችን መናቅ፤ዘረኝነት ወዘተን ማስፋፋት የሚፈቀድ ሊሆን አይችልም:: የድርጅትም ድክመት ጥንካሬ በእብድ እሁድ በአንድ አዳራሽ በሰበሰበው ሰው ቁጥር የሚተመን አይደለም:: በሞቅ ሞቅ ጊዜ፤ እንኳን ሰዉ ወፉ ለውጥን ሲያዜም ከመድረክ ወጥቶ መሪ መሆን ከባድ አይደ ለም--እንዲያውም ለአፈ ጮሌው የሚያመች መሆኑን ከፈረንሳይ አብዮት ጀምሮ በሻለቃ መንግ ሥቱም ታይቷል:: የድርጅት ጥንካሬ የሚገመተው ባለው መዋቅር፤ ዝግጅት፤ ሙያተኛ አሰራር፤ ዲሲፕሊንና ፅናት ነው:: እነዚህን ያጣ ድርጅት ዛሬ ቢገን ነገ ሁናቴው ሲጠጥር የላላ ነውና ይፈርሳል፤ይበታተናል:: በጨለማው ጊዜ ክብሪት መጫር ነው ዋናው:: ሲደይን ከጨለማው አልፎ ኮከብን ማየቱና መፅናቱ::ይህን ሀቅ ስቶ ለድርጅቶች መፈራቀቅና መፈረካከስ ሌላ

አልባሌ ምክንያቶችን መፈለግ በራስ ላይ ቀቢፀ ተስፋን ማስፈን ነው:: የሆነ ድርጅትንም ብቸኛ መሪ ብሎ ማወደስ፤ የሁሉንም የጋራ ጥረትና ትብብር ከመሻት ይልቅ የሌሎችን መፍረስ በመፈለ ግ ክፍፍልን ማስፈንም ጎጂ መሆኑ እየታየ ነው:: ከፖለቲካ እስረኛ አንፃር እንኳን ከእገሌና እገሊ ት ውጪ ሌሎቹ ይደየኑ ይሰቃዩ ብለው ስማቸውን የማያነሱ ንቁ ነን ባዮች ጥቂት አይደሉም:: እኛን ብቻ ደግፉ እንጂ በአጭር ጊዜ  የድል ባለቤት እናረጋችኋለን ብለው ስለ ገፈርሳ ደፈጣ ያወሱንና ዛሬም በየወረቀቱ የወያኔን ወታደር የሚገሉና የሚማርኩልንን አላጣንም:: ውጤቱ ባዶ ሆነ እንጂ!

ደግመን ደጋግመን የሕዝብ ጎራን ድክመት መመርመርና በድፍረት ደክመቶችን አውቆ መፍትሄ መሻቱ ዋና ስራችን ሊሆን የሚገባው ነው:: የሕዝብ ጠላት ማን ለመሆኑ ሕዝብ ምንም ብዥታ የለውምና ነው:: ስለ ወያኔ ፀረ ኢትዮጵያዊነት ነጋ ጠባ መለፈፉ ፋይዳ የለውም-- ዜናነቱ ካከተመ ዓመታት አልፈዋል:: ዋናው ጉዳይ የወያኔ አገዛዝ መወገዱ ነው:: ይህ ደግሞ የማይሆነው ወያኔ ጠንካራ ሆኖ ሳይሆን ተቃዋሚዎቹ ደካማ መሆናቸው፤ ሕዝብ በበቂ ባለመደራ ጀቱና ትግሉ ባለመጠናከሩ የተነሳ ነው:: ለዚህም ነው የላላውን መወጠር ላይ ሁሌም ትኩረት በመስጠት እንደ  ጓያ የሚያሽምደምዱንን በነቂስ እያወጣን እናርም እናስወግድ የምንለው:: ሰዎችን-- ያውም በመከራ በበቂ ሳይፈቱኑ-- ጣዖት ደረጃ አናድርሳቸው፤ ወር የታሰረውን ማንዴላ አንበል ያልነውም ከዚሁ በመነሳት ነበር:: ይህን መገንዘብ ያቃታቸው ግን ገንቢ ጥቆማን በስድብና ዘለፋ ደረጃ ወስደው አቅም ጠፍቶ እንጂ በክብረ ነክ ሊወነጅሉን ቃጥተዋል:: ለነገሩ የሀገር አርአያዎች ሞልተው ባዕዳንን ፍለጋ ምን አስፈለገ ? ስንት ዓመት በእስር የማቀቁ ጀግኖ ቸ የሉንም? እነ አበራሽ ጠፍተው ነው በርማ ድረስ አምሳያ ፍለጋ ጉዞ ያስፈለገው? ከዚህ ባሻገር ወዳጅን ማስፋት ማበርከት በሚል እባብን ወደ ጉያ ማስገባቱ ጅልነት ከመሆኑ ሌላ ሕዝብና ሀገር ን የሚጎዳ ነው ብለን አሳስበናል:: ወዳጅን ማን ጠልቶ ግን ተደናግሮ ጠላትን ወዳጅ ብሎ ማቀፉ ለሞት የሚዳርግ ሆኖብን ነው:: እየተንገዳገደ ያለውን አገዛዝ በሌላ መንገድ እስትንፋስ ሊሰጡት የተነሱና የፖለቲካ ምርጫቸው ያው የአገዛዙ የሆኑ ክፍሎችን ወዳጅ ብሎ ማቀፉ ብልህነት ሳይሆን አንገትን ለአራጅ ማመቻቸት ነው:: በሬ ለአራጁ:: ስልጡን ፖለቲካ ራስን ማጥፋት ሆኖ የተገኘው ለዚህም ነው:: ፖለቲካ ብለው ሀላፊነት የጎደለው ትንተና እያቀረቡ የአስመሳይ ጠንቋ ይ ክታብ-መፍትሄ የሚያቀርቡትም ትግሉን እያዳከሙት ነው:: የወያኔ አገዛዝ ተቃዋሚ ነን ያሉ ትን ማደናቀፉ የሚጠበቅ ነው፤ ጠልፎ ሊጥላቸው መቃጣቱ ለህልውናው አስፈላጊ ነው:: በዚህ ላይ ማማረሩ መፍትሄ አያመጣም:: ዋናው ድክምት ውስጣዊ ነው--ለጠላፊ መመቻቸቱ ነው ጥፋት::

ድርጅቶቸ ራሳቸውን ከጥቃት ሊከላከሉ አልቻሉም:: ድክመቶችን አውጥቶ መፍትሄ መሻት ተገቢ ቢሆንም ገበናን በአደባባይ አስጥቶ ለጠላት ራስን ሰለባ ማድረግ ደግሞ ትግልን የሚጎዳ መጃጃል ነው:: በወንድሜ ግንባር ደም አልይበቱ የከርሞ ወሬ ሆኖ ቀርቶ ሲያሳዝነን ምስጢር

የባቄላ ወፍጮ አይደለም የተባለው ደግሞ ተዘንግቶ የድርጅቶች ውስጣዊ ይዘትና ችግር በራዲዮ ወየ.መ. በወያኔ ጋዜጦች የሚተላለፍ ሆኗል:: በአሁኑ ጊዜ በመግለጫና በድረ ገፅ--ፓልቶክ ሃላፊ ነት አልባ በሆኑ ግለሰቦችአማካይነት የድርጅቶች ገበና ተሰጥቶ ወያኔ እያገላበጠው ነው:: የወያኔ ድረ ገፅ የሆነው አንዱና አዲስ አበባ የሚታተም ሌላ የነሱው ጋዜጣ በተደጋጋሚ የአንድ ድርጅ ትን አሳፋሪ ንትርክና መግለጫ እያተሙ በመቧረቅ ላይ ናቸው:: ሌሎች ደግሞ ተቀዋሚን ደገፍ ን ብለው ተቃዋሚን ሲሰድቡ፤መሪዎችን ሲዘልፉና ክፍፍልን በማስፋፋት ወያኔን ወደዱም ጠሉ ም ሲጠቅሙ እየታዩ ናቸው:: ግርግር ለሌባ ያመቻልና ነውናም የወያኔ ሰርጎ ገቦች አመቺና አመርቂ ክፍተትን አግኝተው አፍራሽ ተልዕኮአቸውን እያካሄዱ ናቸው:: ጥፋቱ የማን? የወያኔ ሳይሆን የድርጅቶቹ የራሳቸው ፤የራሳችን ነው:: ይህ መታወቅና መታመን አለበት:: ቅራኔን አያያዝ አልቻሉም ብለወ የቀድሞዎቹን የሚወቅሱ ዛሬ ራሳቸው ችግራቸውን በውስጣቸው በአግባብ ይዘው በመፍታት ፈንታ የጠላትን ልብ በደስታ በሚሞላ መንገድ በአደባባይ እየተወነጃ ጀሉ ይሰነጣጠቃሉ:: ማን ተጠያቂ? የድርጅትን ምስጢር መያዝ መቻል መጀመሪያ ነው--ለህል ውና ወሳኝ ጉዳይ::

በርካታ በባዕድ ያሉ መጤ ፖለቲከኞች ጥራዝ ነጠቅነትን አዝለዋልና ያሉበት ሀገር የፖለቲካ አየር በኢትዮጵያም የሚነፍስ ይመስላቸዋል:: የኢትዮጵያ አየር መከራና ሰቆቃን፤ላብና ደምን፤ ግፍና ሥቃይን የሚከረፋ መሆኑን ማወቅ ተስኗቸዋል:: ሕዝብ ይላሉ እንጂ የሕዝብ ብሶት ለነሱ ባዳ ነው:: ከብዙሃኑ አንፃር ሲታዩም የደላቸው ሀብታሞችም መሆናቸው መጠቀሱ አግባብ ያለው ነው:: በባዕድ ሀገር ያለው ነፃነት በሀገር ያለ ይመስል ግልፅነት በሚል መርህ የድርጅትን ምስጢር በአደባባይ ሲያሰጡ ወያኔ ተጠቃሚ ይሆናል:: ግልፅነት ብለው ባመጡት ግልብነት ጮሌው ወያኔ ሳሩን ያጭዳል፤ አበባውን ዜጋ ይቀጥፋል፤ ያፍናል፤ያጠቃል:: የድርጅቶች ዕቅዶች በእንጭጩ የሚቀጩበት አንዱ ዋና ምክንያት ይህ ነው--ምስጢር ሊጠበቅ ባለመቻሉ:: የሀገራች ን ትግል በባዕድ ሀገር መድረኮችና ስብሰባዎች፤ በድረ ገፆች ደረጃ ተወስኖ የሚካሄድ ቢሆን ኖር ምስጢር የሚለው መጥበቁ ባላስፈለገ ነበር:: ትግላችንግን በሀገር ቤት ከሆነ (መሆንም አለበትና) በሀገራችን ያለው አገዛዝ ደግሞ አፋኝና ጨፍጫፊ ነውና ምስጢር አልባ ትግል ከንቱ ከመሆኑ አልፎ ሊታገሉ የሚጥሩትን ያስጠቃል፤ ያስገድላል:: እነ እገሌን አደናግረን እንጠቀምባቸውን የይፋ ውይይት እነ እገሌ ራሳቸው እየሰሙት ነው:: ያሳዝናል ወይስ ያስገምታል? ትግልም ሲባል በተደጋጋሚ እንዳልነው አገዛዙ በሚከፍተው በር --ገርበብ ብሏል ብሎ-- ዘው ብሎ ከወጥመድ መግባት ሳይሆን አገዛዙን በሚያስጨንቅና በሚያሽብር ደረጃ ትግልን ማካሄድ ነው:: በኑሮ ውድነ ት ዙሪያ በደቡብ አፍሪካ በሰሞኑ የተካሄደው ትግልና አድማ የቅርብ ምሳሌ ነው:: የእኛዎቹ የኑሮው ውድነት ሳይነካቸው ቪላ ሲገነቡ ሲገዙ ማየት ተገደናል:: ለዚህም ነው ሕዝብ የራሱን ስርየት በራሱ ለማስፈን ሕዝብ ቢጭኑት አህያ ቢወጡበት ፈረስ ሆኖ መገኘት ማቆም ያለበት:: ለጭቆናና በደል ቻይነትና ትዕግስት የሰውን ልጅ ሰብዕና ይፃረራል:: ለዚህም ነው ሕዝብ ጠላቱ ን ማወቅ ብቻ ሳይሆን ባለው አቅምና ችሎታም ጠላቱን ማቸነፍ እንደሚችል እምነት እንዲኖረ ው ማድረግ የሚገባው:: ጠላትን መጥላት ብቻ አይበቃም--ጥላቻን መሰረት አደርጎ ታግሎ

ማስወገድ ያስፈልጋል። ምን አቅም አለን እቅሮ እሮሮ ስህተት ነው። ኃይል የሕዝብ ነው የሚለ ው ባዶ መፈክር አይደለም። ሕዝብ በተደራጀ መልክ አገዛዙን ማሽመድመድ ይችላል። በቅርቡ አንድ ተቃዋሚ በሉኝ ባይ የወያኔ አገዛዝ አባል የነበረ ግለሰብ የኢትዮጵያን ጦር አትከፋፍሉ ብሎ ሊያስጠነቅቅና ሊመክር ሲሞክር ተደምጧል። በዚህም ሰልፉ ከማን ጋር መሆኑን ዳግም አረጋግጧል። በተገላቢጦሽ ነው ሀቁ--ሕዝበ ድልን ይቀዳጅ ዘንድ ወይም ለማሸነፍ የወያኔን ጦር ና የአፈና ኃይል መከፋፈልና አቅመ ቢስ ማድረግ ያስፈልገዋል። ወታደሮችና መኮንኖች ለወያኔ መታዘዝን ትትው ከሕዝብ ጎን እንንዲሰለፉ፣ እንዲያምፁ መቀስቀስም ግዳጅ ነው። የወያኔ ፀረ ኢትዮጵያ አገዛዝ በሥልጣን ያለው በአፈና ሀይሉና ጦሩ በመጠቀም ነውና ይህን መመኪያውን መከፋፈልና ማዳከም የትግላችን ዋና ስራ ነው። ወያኔው አጉል ተቃዋሚ በመሰረቱ የወያኔ ስርዓ ት እንዲቀጥል ፈላጊ ነውና ጦሩን አትከፋፍሉት የሚል መሰሪ ጥሪውን ለሀገር ያሰበ መስሎ አስደ ምጧል። የሀሳዊ መሲህ መፈክሮች ብዙ ናቸው። ነቅተን ሀቀኛውን ከአደናጋሪው መለየት መቻል አለብን።

በትግል ለተሰማራ ወይም ሊሰማራ ለቆረጠ ሕዝብ፣ ከፊቱ ፅልመት የሆነ አረመኔ ጠላት ለተገደገ ደበት ሕዝብ ከግቡ ለመድረስ ሲነሳ አንዱ ትጥቁ ታሪኩ ነው። በደም የተገበየውን ታሪክና ቅርስ የራሱ ማድረግ አለበት። ታሪኩን ማስከበር ይገበዋል። የኢትዮጵያ ጠላቶች በሞላ በቅድሚያ ሩምታቸውን የሰደዱት በሀገራችን ታሪክ ላይ ነው--የዚህን ሀቅነት ከሙሶሊኒ ግራዚያኒ ጊዜ እስከ ወያኔና ጠባቦች ዘመቻ ያየነው ነው። ታሪከን በአንድነት ማጠናከሪያና መሰረትነት መጨበ ጥ ማስከበር ከተቻለ የሕዝብ የጋራ ትግል እውን ይሆናል። ከጥንት ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ደግሞ ስንቱ ጀግና ሕይወቱን የለገሰበት/የለገሰችበት መራራ ትግል ተካሂዷል። ብዙ ተመክሮ ተገብይቷል። ይህን ሰፊ ተመክሮ የሚያክቸለችሉ ሕዝብን ቅርስ ያሳጠታል፣ ትጥቅ አልባ ያደርጉታል። ከድልም ከሽንፈትም፣ ከድክመትም ጥንካሬም እንዳይማር አድርገውና አውረው ለአረመኔ ጠላት እርቃኑን አጋልጠው ይሰጡታል። ለዚህም ነው በበኩላችን የታሪክ ቅርስና ሀቅን በተመለከተ ከሀሰት ነጋዴዎች ጋር ግብግብ የቀጠልነው። የተሰዋው ትውልድ ቅርስ ለሚታገለው የዛሬው ትውልድ ትጥቁ ነው። የአሁኑ ወቅት በርካታ ፖለቲከኞች የሀገራቸውን ሳይሆን የባዕዱን ታሪክና ቅርስ ያውቃሉ። ትላንት የተካሄደውን ትግል በተመለከተ ያላቸው ግን ዛቤ ገለባ ነው። በመሆኑም የወያኔን መሰረታዊ ይዘት በተመለከተ፣ ወያኔን ከውልደቱ ጀምሮ በመታገል የተከፈለውን ዋጋ፣ ማን ኢትዮጵያን ሲያደማ እንደነበር ወዘተ የሚያውቁት የለም ማለት ይቻላል። የድርጅት ሰፊ ተመክሮ እያለ የትላንቱን ስህተት ይደግማሉ። አስመሳዩና በተለ ምዶ አነጋገር የመንደሩን አውደልዳይ በቆራጥ መሪነት ይወስዳሉ። መራራው ትግል ምሬቱ ምን ላይ መሆኑን አያወቁም፣ ለማወቅም አይፈልጉም። ለማወቅ ከመጣር በፊት አውቀናል ብሎ ሰበካ መጀመሩን ይመርጣሉና የተባ ምላሳቸው ብረት መጨበጥን ይተካል። በአጭሩ ስለ ትግል የማያውቁ የትግል ቅኔ ሊያስረዱን ቦታ ይይዛሉ። ይህ መቆም አለበት። ይህን ስንል ደግሞ ያው እንደተለመደው እኛ ብቻ አዋቂ ብለው ተሰይመው ሰደቡን የሚሉ አይጠፉም። ይህ

ድምጻሜ ስህተት ነው፡፡ ገንቢ ሂስና ጠቃሚ ጥቆማ የሚያቀርብ ወዳጅ እንጂ ጠላት አይደለም፡፡ አማርኛነቱ አጠያያቂ ቢሆንም በእውነት ከሀገር አንታገል ካልን “ መማማር” አለብን፡፡ ሁሉም የሚያውቀውንና ተመክሮውን ማስተላለፍ አለበት፡፡ የዚያ ቆራጥ ትውልድ ተመክሮ በሆነ ምክንያት የሚጎመዝዛቸው ካሉ ከቅርቡ ከ1997 ምርጫና ትግል እንኳን ብዙ ተመክሮ በመገብየ ት ዳግም ከመሰል ስህተት ሊርቁ ይችላሉ፡፡ ለቀጣዩ ትግል ምን መንገድ፤ በነማን መሪነት ለሚለውም አሁን እየተሰጠ ካለው መልስ የተሻለና የተስተካካለ መልስ መስጠት ይቻላቸዋል፡፡ አለበለዚያ ስህተት እየተደጋገመ ፤ግርግሩ እየደመቀ ፤ አስመሳዮች መድረክ እየነጠቁ፤ ወዳጅ ያልሆነው እየታቀፈ ፤ድርጅቶቹም በአደባባይ ራሳቸውን አያቀለሉ፤ እየተነካከሱ ብስጭትና ቀቢፀ ተስፋ ይሰፍናል፡፡ መክፈልት ሲሉ መቅሰፍት፡፡ ጠላታቶቻንም ይፈነድቃሉ፡፡

ለዚህም ነው ሰነፍ ቢመክሩት ውሀ ቢወቅጡት ከመባል ያድነን ማለት የተገደድነው፡፡